Calgary

# የ COVID-19 ክትባት መረጃ

## አሁን በነፃ የሚሰጡ የ COVID-19 ክትባቶች ክትባቱን ለመውሰድ ብቁ ለሆኑ የካልጋሪ ነዋሪዎች ተዘጋጅተዋል

ስለ ክትባቱ ጥያቄዎች ቢኖርዎት ምንም አይደለም ። ትክክለኛውን መረጃ ከሐኪምዎ ወይም እንደ Health Canada እና Alberta Health Services (AHS) ካሉ አስተማማኝ ምንጮች ያግኙ። ስለ ክትባት ጥቅሞች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **canada.ca/vaccines** የሚለውን ድረ ገፅ ይጎብኙ ፡፡

የአልበርታ ግዛት ክትባቱን በመጀመሪያ ለከባድ ህመም ተጋላጭ ለሆኑ ሰዎች ይሰጣል ፡፡ከዚ ቀደም የቆየ ህመም ካለዎት **alberta.ca/vaccine** የሚለውን ድረ ገፅ ይጎብኙ ወይም ዶክተርዎን አለበለዚያም የፋርማሲ ባለሙያዎን ያነጋግሩ።

ክትባቱን ለመውሰድ ብቁ እንደሆኑ ወዲያውኑይከተቡ ፡**alberta.ca/vaccine** የሚለው ድረ ገፅ ላይ በመግባት መቼ ለክትባቱ ብቁ መሆንዎን ይወቁ። ትክክለኛ የጊዜ ሰሌዳዎች ባለው የክትባት አቅርቦት ላይ ይወሰናሉ

## ክትባት መውሰድ ያለብዎት ለምንድን ነው?

ክትባቶች በሽታዎችን ለመከላከል እና ለመዋጋት የሚረዱ ፀረ-እንግዳ አካላትን በመገንባት በሰውነታችን ውስጥ ያለውን በሽታ የመከላከል ስርዓታችንን የበለጠ ያጠናክራሉ ፡፡ COVID-19 አዲስ ቫይረስ ስለሆነ ማንም ሰው ለበሽታው ተፈጥሯዊ መከላከያ አቅም የለውም ፡፡ በበሽታው ከመያዝ ይልቅ ክትባቱን መውሰድ በጣም ደህንነቱ የተጠበቀ እና የበለጠም ውጤታማ ነው ፡፡

ክትባቱ የሚወሰደው በፈቃደኝነት ነው ነገር ግን መከተብ የራሳችንን እና የሌሎችንም ደህንነት ይጠብቃል እናም ቶሎ ወደ ተለመደው የህይወት እንቅስቃሴ መመለሳችንን ያረጋግጣል ፡፡ በበሽታው እንዳይያዙ ለመከላከል እና በበሽታው ከተያዙ ከበድ ያለ ህመም እንዳይታመሙ ሊረዳዎ ይችላል



## መከተብ ያለበት ማነው?

**ለክትባቱ ብቁ የሆነ ማንኛውም የአልበርታ ነዋሪ መከተብ አለበት ፡፡** ከ ኮቪድ-19 ካገገሙ እንኳን በሽታ የመከላከል አቅምዎን ከፍ ለማድረግ ክትባት መውሰድ ይኖርብዎታል ፡፡

የአልበርታ የጤና እንክብካቤ ካርድ ከሌለዎት አሁንም ክትባቱን መውሰድ ይችላሉ ፡፡ ቀጠሮዎን ለመያዝ በ 811 ይደውሉ ፡፡

ክትባቱን ለመውሰድ የካናዳ ዜግነት አያስፈልግዎትም። መታወቂያ ብቻ በቂ ነው ።ተቀባይነት ላለው መታወቂያ ዝርዝር **alberta.ca/vaccine** የሚለውን ድረ ገፅ ይጎብኙ።

## ከተከተቡ በኋላ ምን ይከሰታል?

አብዛኛዎቹ የአልበርታ ነዋሪዎች በክትባቱ ከበሽታው እስኪጠበቁ ድረስ ሁሉንም የ ጤና ጥበቃ መመሪያዎች መከተል መቀጠል አለብን

- ጭምብል ያድርጉ;
- 2 ሜትር ርቀትን ይጠብቁ;
- እጅዎን ይታጠቡ; እና
- ህመም ሲሰማዎት በቤትዎ ይቆዩ ፡፡

ለሁለተኛው ክትባት ብቁ ሲሆኑ AHS ያሳውቅዎታል ፡

## ድጋፍ

- የበሽታ ምልክት ካለብዎ በቤትዎ መቆየት አለብዎት እና ምርመራ ማድረግ አለብዎት ፡፡ ምርመራውን በኦንላይን ቀጠሮ ለመያዝ **alberta.ca/COVID19** የሚለውን ድረ ገፅ ይጎብኙ ወይም 811 ላይ ይደውሉ።
- በህመም ፣ ራስዎን አግልለው በማቆየት ወይም ራሱን ያገለለን ሰው የሚንከባከቡ በመሆኑ ምክንያት መሥራት ካልቻሉ የገንዘብ ድጋፍ ሊገኝ ይችላል። ለበለጠ መረጃ **811** ይደውሉ ፡፡
- በ COVID-19 ምክንያት ራስዎን አግልለው ማቆየት ካለብዎት እና በገዛ ቤትዎ ውስጥ ይህን ማድረግ ካልቻሉ ነፃ የሆቴል ክፍሎች እና የገንዘብ ድጋፎች ይገኛሉ። ለበለጠ መረጃ በ **211** ይደውሉ ፡

## እርዳታ ይፈልጋሉ?

ለክትባቱ ብቁ መሆንዎን ለማወቅ በ **811** ይደውሉ እና ቀጠሮ ይያዙ ፡፡ አገልግሎቱ በ 240 ቋንቋዎች ይገኛል ፡፡

በራስዎ ቋንቋ የ COVID-19 ድጋፍ ከፈለጉ **1-833-217-6614** ላይ ይደውሉ ፡፡

## የሚያደርስዎ መኪና ይፈልጋሉ?

ወደ ክትባት ቀጠሮዎ የሚወስዱ እና የሚመልሱዎት ተሽከርካሪዎችን ለማግኘት እርዳታ ከፈለጉ በ **211** ይደውሉ ፡፡

21-0013015 ADV-8884